የጎንደር ሕብረት

gonderhibrert72@gmil.com /website: www.gonderhibret.org

December 8, 2015

## የጎንደር ባታ እስር ቤት ቃጠሎ ፤ የወያኔ የግፍ ሥራዓት ማብቂያ ምልክት ነዉ!

በቅድሚያ፤ ለሰው ልጅ ህሊና እጅግ ከባድ የሆነውን፤ ከሞት ቅጣትም እጅግ አስከፊ፤ ወገን በወገኑ ላይ ሊወሥድ ይችላል ብሎ መገመት የሚያቅተንን፤ በተለይም ከኢትዮጵያውያን ስነ ባህሪ ውጭ የሆነውን እና አውሪያዊ ባህሪን በተላበሰ መልኩ፤ በወግኖቻችን ላይ የተወሰደውን በእሳት ማቃጠል አረመኔ ተግባር እያወገዝን፤ የተሰማንንም ልብ የሚያደማ ጥልቅ ሃዘን ስንገልጽ፤ በዚህ ተግባር የተሰማሩ አረመኔ ወታደሮች ይሁኑ አዛዥ አለቆቻቸው፤ ጊዚያቸውን ጠብቀው፤ በሰፈሩት ቁና እንደሚሰፈርባቸው አንጠራጠርም።

በዚህ እሥር ቤት ለረዥም ጊዜ ሲማቅቁ የነበሩ ወገኖች፤ አገራቸው ሳይወዱ እና ሳይፈቅዱ ወደ ትግራይ በመከለሉ ምክንያት ሰላማዊ ትግል ይታገሉ የነበሩ የወልቃይት ጠገዴ እና የማይፀምሬ አዳርቃይ ተወላጆች፤ እሱ ምርጫ ብሎ የሚጠራውን፤ ለኛ ግን ቅርጫ የሆነውን መድረክ ለመፈታተን በሰላማዊ መንገድ ይታገሉ የነበሩ እና መጨረሻቸው እስር ቤት የሆነው፤ በአጠቃላይ አብዛኛወቹ ክወያኔ የወረራ ዘመን ጀምሮ በፖለቲካ እምነታቸዉ እና በዘራቸዉ ምክንያት ታስረዉ በግፍ ሲሰቃዩ የነበሩ ወገኖቻችን ናቸዉ ሰሞኑን በጎንደር ባታ እስርቤት የተቃጠሉትም ሆነ፤ ከእሳት ለማምለጥ ሲሉ በመትረየስ የተጨፈጨፋት ። በተለይ በአሁኑ ሰዓት አብዛኛዉን የጎንደርን፤ የወሎን የአፋርን መሬት እየነጠቁ በጉልበት ለታላቋ ትግራይ ቆርጠዉ ወሰደዉ "የግፍ ግፍ ከእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" ሆነና የዉጭ አገር ተባባሪ በመሆን 1600 ኪሎሜትር የኢትዮጵያን ለምና ሰፊ መሬት ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት እያወጀ ባለበት ወቅት የጎንደር ህዝብ አመጽ እንዳያነሳ፤ ግራ ለማጋባት እና ተቃዋሚ ድርጅቶች የወሰዱት የጭካኔ እርምጃ ለማሥመሰል ወያኔ የወሰደው አረመኒያዊ ተንኮል ነው። በጎንደር ህብረት እምነት፤ የሰውን ህይወት በእሳት ማቃጠል፤ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ያልተለመደ ጭካኔ እና ኢ-ሰባዊነት ከመሆኑም በላይ፤ ከእሳት ሊያመልጡ የሞከሩትን፤ በጥይት መደብደብ፤ የሰው ልጇ ሊወሸከመው የማይችል አረመኔያዊ ተግባር ነው። ምንም ይሁን፤ ምን! በሰበባ ሰበቡ በወያኔ የታሰሩ ሁሉ ወንጀለኞች አይደሉም። ደማቸውም እንደ አቤል ንጹህ ደም፤ በገዳዮች ህሊና እስከ እልፊተ ሞታቸው እየጮኽ ሲያባንናቸው ይኖራል። እኛም የነዚህን ንጹኃን ወገኖቻችንን ደም ጠጭዎች ለፍርድ ለማቅረብ እና ሰቆቃቸውን ለማንኮታኮት፤ የበለጠ

ቆርጠን በሕብረት እንድንነሳ ግድ ይለናል። ወያኔ ቀን ከቀን፤ ግፍ እና በደሉን የማያቆም አረመኔ አገር በቀል ጠላት ነውና።

በሌላ በኩል ከጎንደር ባታ እሥር ቤት ቃጠሎ የግፍ እስረኞችን ህይወት ለማዳን የተረባረበዉ ጀግናዉ የጎንደር ህዝብ ያደረገዉ ሰባዊ እና ወገናዊ ፍቅር የተሞላበት የአብሮነት ህይወት የማትረፍ ትብብር እጅግ የሚያኮራ ታሪካዊ ሥራ ልናደንቅ እንወዳለን።

ከእስር ቤት ያመለጡ ወንድሞች/ እህቶቻችን ከእንግዲህ ቀሪዉን ህይወታቸዉን ፍትህ እና ነፃነት የነገሰባት ኢትዮጵያን ለማየት መታገል ይጠበቅባቸኋል። ወያኔን ለማንበርከክ በቁርጠኝነት ህዝባዊ ትግሉን ለማጎልበት ተደራጅታችሁ አረመኔዉን መንግስት ለመጣል የንቅስቃሴዉ አካል እንደምትሆኑ ሙሉ እምነታችን መሆኑን እየገለጽን፤ በዘራችሁ እየተዋረዳችሁ በግርፋት ከምትሰቃዩት እስርቤት በመዉጣታችሁም ደስታችን እናበስራለን።

የመላዉ ኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ! ሰፊዉ አራሽ ገበሬ፤ ተማሪና አስተማሪዉ፤ መለዮ ለባሹ ጭቁን ወታደር። ወያኔ በድብቅ  በጎንድር፣ በጎጃም፤ በወለጋ ኢሊባቡር፤ ከፋ እና በጎምጎፋ አካባቢ ያለዉን የጠረፍ ለምና ሰፍ መሬት  እንግሊዞች በቅኝ ግዛተ ዘመናቸው በህገወጥ ያሰመሩትን የቅኝ ግዛት ካርታ እንደ እውነተኛ ታሪክ በማሥመሰል ለሱዳን አሳልፎ ለመስጠት የሚያደርገዉን ሴራ፤ ለማክሸፍ በወጣቱ ትዉልድ አስተባባሪነት ከዳር እስከዳር በቁጣና በቁጭት አደባባይ ወተህ ተቃዉሞህን አሰማ። አገርህን የሚሸጥ ቡድን መሪህም መንግስትህም አይደለም። በተለይ ወታደሩ፤ የአገርህን ዳር ድንበር ማሥከበር ሙያዊ ባህሪህ ነውና መሳሪያህን በጠላትህ ላይ አነጣጥር። በአሁኑ ሰዓት፤ ጎንደር ላይ ትግርኛ ተናጋሪ ታጣቂ ብቻ ህግ አስከባሪ ሁኖ ሲመጣ ማየት፤ ሌላዉን ኢትዮጵያዊ መለዮ ለባሽ አለማመን መሆኑ ግልጽ ነዉ። አንተም ጭቁን ከህዝብ አብራክ የወጣኸዉ ሰራዊት፤ ከፋፋዩን ወያኔ በቃህ በለዉ። የትግራይ ነጻዉጭ ግንባርን ፈርተህ ቁጭ ባልክ ቁጥር ግፉን ያበዛዋል፤ ስትበረታ ደግሞ፤ የርጎ ባህር ለማሳየት የማይጨበጥ ዉሸት ይዘላብዳል። በመፍራት የወያኔ መከራ ማክተሚያ የለዉም።  የወያኔ አመራሮች፤ በሰዉ ፍጡርነት ደረጃ የሚመደቡ አይደሉም፤። ፈርተን ስንሸሽ አሳድደዉ የሚነክሱ ዉሻዎች ናቸዉ። ስንጠነክር የሚፍረከረኩ የሌባ ጭንብል የተላበሱ የባእድ አይምሮ የተሸከሙ አሳፋሪ ትዉልድ ናቸዉ፤ እነሱን መፍራታችን እጅግ

**አዋርዶናል። ሥለፈራህ ወያኔወች አይምሩህም። ብትቀርባቸውም፤ ትግርኛ ተናጋሪ ካልሆንክ አያምኑህም። በአሁኑ ሰዓት ጠንክረህ በመታገል ነፃ ልትወጣ ይጠበቅብሃል።**

**በመጨረሻም በማንኛዉ ጉዳይ የጎንደር ህብረት ከጀግናዉ የጎንደር ህዝብ ጎን መሆናችን እየገለጽን፤ ከአሳት ሲያመልጡ በወያኔ ተጨፍጭፈዉ ህይወታቸዉን ላጡት እና ቅማንትና አማራን ለማካለል በሚል ወያኔ በለኮሰዉ ጦርነት መስዋዕት ለሁኑ የሟች ቤተሰቦች እግዚአብሄር መጽናናትን ይስጥልን  እንላለን።**

**ከፋኝ! ያለን ህዝብ ትግል ማስቆም ፈጽሞ አይቻልም!**

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

**የጎንደር ሕብረት።**